# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

ፕሮግራም፡- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ
**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ሰኔ 5-6 ቀን 2002 ዓ.ም**

**የወያኔ ቡድን በድንጋጤ የአዲስ አበባን ህዝብ አጣብቂኝ ውስጥ ሊያስገባ መሆኑ ተጋለጠ፤**

**አንድ የምክር ቤት አባል የወያኔን ገመና አጋለጡ፤**

**የወያኔ ቡድን አጋር ድርጅት ከፍተኛ አመራሮችን አባረረ ለእስራትም ዳረጋቸው፤**

**ሰኔ 1 ቀን የሰማዕታት ቀን ተከብሮ ዋለ፤**

**ለሙዋቾች የሰማዕታት ሐውልት እንዲሰራላቸው ተጠየቀ፤**

የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት ባወረዱት መመሪያ መሰረት የአዲስ አበባ ምክር ቤት ሰሞኑን አስቸኳዋይ ስብሰባ አድርጎ የመስተዳደሩን መዋቅር የሚያሻሽል ህግ ማውጣቱ ታወቀ::

በፍርሀት ውስጥ ተዘፍቆ ያለው የወያኔ ቡድን በየጊዜው አዳዲስ ስልቶችን እየተጠቀመ ያለ ቢሆንም በቅርቡ ግን የአዲስ አበባን ህዝብ በጠበቀ ሁኔታ ለመቆጣጠር የመዋቅር ለውጥ ማድረጉ ታውቆዋል::

በዚህም መሰረት ለብዙ ዓመታት የአዲስ አበባ ከተማ በ99 ቀበሌዎች ተከፋፍላ ስትተዳደር የቆየች ብትሆንም በቅርቡ በ2002 ዓ. ም በተደረገ ምርጫ ውጤት ጋር በተያያዘ የከተማዋ ነዋሪዎችን ለመቆጣጠር እንዲያመች በ116 ወረዳዎች በመከፋፈል ለአገዛዙ እንዲያመች አድርገው ማዋቀራቸው ታውቆዋል::

የአዲስ አበባ ከተማ የምክር ቤቱ መሰብሰቢያ ዋነኛ አጀንዳ በዘንድሮው ምርጫ ውጤት ላይ ያተኮረ እንደነበር የጠቆመው የደረሰን ዘገባ በተለይ በአዲስ አበባ የተገኘው ውጤት አስጊ እንደነበር በመጥቀስ ከሁለት ዓመት በሁዋላ የከተማዋ ምክር ቤት የሚመረጡበት በመሆኑ አሁን ባለው ተጨባጭ እውነታ ሊሸነፉ እንደሚችል በማወቃቸው ከወዲሁ ልክ እንደ ዘንድሮ ምርጫ መዘጋጀት እንዳለባቸው መወያየታቸውን ታውቋል::

ወያኔ በሀገር ሀብት እና በህዝብ ገንዘብ እንዳሻው ሲረጭ እና ሲበትን የነበረ ከመሆኑ ጋር የተገኘው ውጤት እጅግ አናሳ በመሆኑ ያጋጠሙ ችግሮች እና የተገኙ ውጤት በሚል አንዱ የመወያያ አጀንዳ ሆኖ እንደዋለም ታውቆዋል::

በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት አዳራሽ ውስጥ በተደረገው በዚሁ ስብሰባ ላይ ኩማን ደመቅሳን ጨምሮ ሌሎች የከተማዋ ባለስልጣናት የተለያዩ ጥያቄዎችን እና ሀሳቦችን የሰነዘሩ ከመሆኑም በላይ ዘንድሮም ከአዲስ አበባ የተገኘው ውጤት እጅግ አስደንጋጭ ብቻ ሳይሆን ህዝቡ ጥላቻውን የገለፀበት በመሆኑ የእኛን ስህተት መፈተሽ ግድ ይላል ያሉት አንድ የምክር ቤቱ አባል አሁንም የተሰወሩና የተደበቁ እውነቶች ስላሉ እሱን እስካላወቅን እና እስካላገኘን በስተቀር በሽንገላ መጉዋዙ ውጤት እንደሌለው በድጋሚ ዘንድሮም አሳይቶናል ሲሉ ገልፀዋል::

በህዝቡ ላይ እየደረሰ ያለውን የፖለቲካ፤የማህበራዊና የኢኮኖሚ ጭቆና ማስወገድ እስከ አልተቻለ ድረስ ምንም ብንለፋ...... ምንም ሰርተን ብናቀርብ ውጤት አያመጣም ያሉት እኚሁ ግለሰብ አሁንም እዚህ ምክር ቤት ውስጥ የሚታየው እንዳለፈው ጊዜ ሁሉ ሽፋፍኖ ለማለፍ እንጂ ህዝቡ ችግሩ ምንድነው? በሚል ለማየት ሲሞከር አላየሁም ሲሉ ተናግረዋል::

ምርጫ መመዝገቤን እና ውድድር ውስጥ መግባቴን የሰፈር ሰዎች ፎቶዬን አይተው ነግረውኝ ነው ያሉት እኚሁ የህግ ባለሙያ እኔ እዚህ ምክር ቤት ተመርጬ የመጣሁት ፍጹም በማላውቀው መሆኑን ሁላችሁም ባትሆኑ ጥቂቶቻችሁ ታውቃላችሁ ስለዚህ ይሄን እንዲህ ያለ ስራ ሲሰራ ከእኔ ከባለጉዳዩ ጋር ተነጋግሮ ቢሆን ይመረጥ ነበር ካሉ በሁዋላ አሁንም ከህዝቡ ጋር ሆድ ለሆድ ሆነን ተገናኝተን ካልሰራን መጪው ውጤትም ተመሳሳይ ውድቀት ነው ሲሉ በምሬት ተናግረዋል::

የእሳቸውን ንግግር ተከትሎ ከፍያለው የተባለው የብአዴን ከፍተኛ ባለስልጣን የአዲስ አበባ ምክር ቤት ምክትል ፕሬዝዳንት አሁን እሳቸው ያሉት ነገር ለእኛ ለምክር ቤቱ የማይመጥን እና ተራ ነገር ከመሆኑም በላይ በግዴታ ተመርጬ ነው ብለው ካሉ የምክር ቤት አባልነታቸውን በፍቃዳቸው ለመልቀቅ የሚከለክላቸው የለም ሲል በቁጣና በንዴት  መናገሩን የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

ስብሰባው ከተጠናቀቀ በሁዋላ ከፍያለው አዘዘ የተባለው የብአዴን ታጋይ እቢሮው አስጠርቶ «መላ የምክር ቤቱ አባላት በተሰበሰቡበት እና ጋዜጠኞች በተገኙበት ቦታ ይህን አይነት ነገር መናገርዎ እጅግ ከባድ ወንጀል ነው፡፡በመሆኑም ከዚህ በሁዋላ እንዲህ አይነት ድርጊት ቢፈፅሙ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድብዎ ይደረጋል» ሲል እንዳስፈራራቸው የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል፡፡

ወያኔ አንዱን እየሾመ ሌላውን እየሻረ የስልጣን እድሜውን ማራዘሚያ አድርጎ የቆየ ቢሆንም ከጥቂት ጊዜ ወዲህ በተለይ አንጋፋዎቹ በጡረታ ይሰናበታሉ ተብሎ መግለጫ ከተሰጠ በሁዋላ የወያኔ አጋር ድርጅት የሚባሉት ውስጥም ትርምስ መፈጠሩ ታወቀ፡፡

የራሴ ናቸው የሚላቸው በረሀ ቀመስ ታጋይ ናቸው የተባሉት ግለሰቦች የሚመሩት አራት ድርጅቶችን ጨምሮ በሀገሪቱ በብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሰረቱ ድርጅቶችን አጋር አድርጎ በስሩ የጠቀለላቸው ጭምር በውስጣቸው ችግር እየተፈጠረ መሆኑን ከሚደርሱን ጥቆማዎች ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

የሐረሪ ብሔራዊ ሊግ ተብሎ የሚታወቀው የወያኔ ደጋፊ ድርጅት ውስጥ ያሉ ከፍተኛ ባለስልጣናት መሀከል በተፈጠረ አለመግባባት ድርጅቱ ለሁለት የተከፈለ ከመሆኑም በላይ ባለስልጣናቱ እየተባረሩ መሆኑንም የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡

ሁል ጊዜ ጥገኛ ሆነን የምንኑዋዘው እስከ መቼ ነው?የሚል ጥያቄ እንዳቀረበ የተነገረው የሀረሪ ሊግ ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ከስልጣኑ እንዲባረር ከመደረጉም በላይ የግለሰቡ የሀሳብ ተጋሪ ናቸው የተባሉ አምስት ባለስልጣናትም ተመሳሳይ እርምጃ እንደተወሰደባቸው ለማወቅ ተችሎዋል ፡፡

የፓርቲው የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ  አቶ ራይድ አብዱልቃድር የተባለው ነባር ከፍተኛ አመራሩ ከስልጣን የተባረረው የእጅ አዙር የወያኔን ቅኝ ግዛት ክፉኛ በመኮነኑና ሌሎችንም አባሎች በማሳመኑ ነው ያለው የደረሰን ጥቆማ በተመሳሳይ በጋምቤላ ክልል ውስጥም እንደዚሁ የማንነት ጥያቄ ባነሱ ተወላጅ ባለስልጣናት ላይ የእስራት እና የማባረር እርምጃ እንደተወሰደባቸው ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ወያኔ ከውስጥ እና ከውጭ አጣብቂኝ ውስጥ ወድቆ ባለበት ጊዜ የወያኔ አጋር ድርጅት መሪዎች ናቸው የሚባሉት የወያኔ ቅኝ አገዛዝ ይብቃን ጥያቄ ማንሳታቸው ከጀርባቸው አንድ የሚገፋፋ እና የሚያስተባብር ኃይል አለ በማለት የወያኔ ባለስልጣናት መለስ ዜናዊ፤ በረከት ስምኦን እና ሌሎችም በየፊናቸው በየድርጅቶቹ ውስጥ የምንጠራ ዘመቻ መጀመራቸው የበለጠ ነገሩ ትኩረት እንዲያገኝ እና በአባላቶቻቸው ዘንድ ጥይቄ ማስነሳቱም  ጨምሮ የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል፡፡

አሁን የተጀመረው ምንጠራ በቀጣይም ማዕዳቱ ይቀጥላል በሚል እርስ በርስ እየተተራመሱ ያሉት የወያኔ አጋር ድርጅት የሚባሉት የጥቂት ግለሰቦች መንደላቀቂያ ፓርቲዎች በህዝቦች ደምና እንባ ወያኔ ሲጨፍር አብረው እየጨፈሩ በመሆናቸው ከእንግዲህ አንፈልጋቸውም በማለት ይፋ ተቃውሞ ባሰሙ የጋምቤላ ክልል ባለስልጣናት ላይ የእስራት እርምጃ የተወሰደባቸው ሲሆን ጠቂቶቹ በሱዳን በኩል ወደ ውጭ መሰደዳቸውንም የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

ግራ ተጋብቶ የሚይዘውን እና የሚጨብጠውን ባጣበት በዚህ ወቅት የኔ ናቸው የሚላቸው አጋር ድርጅት መሪዎች እና ነባር የበረሀ ሰዎች የሚያነሱት ጥያቄ ራስ ምታት እንደሆነበት የጠቆሙት ምንጮቹ በተለይ የበላይ ከፍተኛ ባለስልጣናት መለስ እና ጥቂት አሽቃባጮቹ በሚሰሩት ስራ እየተበሳጩ እንደሚገኙ ይሄው የደረስ ጥቆማ አብራርቶዋል::

በተለይ ባለፈው ወር ስራ አስፈጻሚዎቹ አስቸኳዋይ ስብሰባ አድርገው የሀገሪቱን ስልጣን ሙሉ በሙሉ ለመለስ አስረክበው መስጠታቸው እያበሳጫቸው ሲናደዱ እየተደመጡ መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል::

የወያኔ አምባገነን እና ዘረኛ ቡድን ሰኔ 1ቀን 1997 ዓ.ም በአዲስ አበባ መንገዶች ላይ በጭካኔ ያለ አንዳች ጥፋት ከ197 በላይ ንፁሀን ዜጎችን በግፍ የጨፈጨፈበትን ለማስታወስ የሰማዕታት ቀን ተከብሮ መዋሉ ታወቀ::

5ኛ ዓመት የሰማዕታት ቀን የሙዋች ቤተሰቦች በህብረት ተሰባስበው በመኢአድ ቢሮ ውስጥ በመገኘት የሻማ ማብራት ስነ ስርዓት እንደተካሄደ ለማወቅ ተችሎዋል::

ዕለተ ሐሙስ 1997 ዓ.ም ከጠዋቱ 2 ሰዓት ሲሆን አዲስ አበባ በተቃውሞ ሰልፍ ትናጥ ጀመረች::ሰራተኛው ወደ ስራው.....ተማሪው ደብተሩን ሸክፎ ወደ ትምህርት ቤት ......ቀን በሌው ወደ ስራው ሲጉዋዝ ድንገት ሳይታሰብ አገር አማን ነው ባሉ ንፁሀን ዜጎች ላይ ቅልብ የወያኔ አግአዚ ጦር እና የፌዴራል ፖሊስ በህብረት በመትረየስ እና በስናይፐር ማጨድ ጀመሩ::

መግቢያና መውጪያ ቀዳዳ የጠፋቸው ህጻን፤ አዋቂ ፤ሴት ፤ወንዱ እየተራወጡ መሸሸጊያ ቦታ እስኪያገኙ ድረስ ቅልብ ቅጥር ነፍሰ ገዳዮቹ እየተከተሉ መልቀም ጀመሩ::እናም በአንድ ቦታ ከ20 ሰው በላይ እየወደቀ እዚያው ያሸልብ ጀመር::

በአዲስ አበባ ከተማ በተለይ አዲስ ከተማ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ አውቶቡስ ተራ..... መርካቶ...... አምስተኛ እና ሰባተኛ ተኩሱ ቀለጠ::ምድር ቀውጢ ሆነች::እዚያም እዚህም አስከሬን እየወደቀ ለማንሳት የሄደው ሁሉ እዚያው ተመትቶ ሲወድቅ ማየት ቀላል ነገር ሆነ::

በዚያች እለት ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም ዕለተ ሐሙስ በተፈጸመ አረመኔያዊ ግድያ ወደ ትምህርት ቤት በመሄድ ላይ የነበሩ ተማሪዎች እየተለቀሙ ሲገደሉ ያዩ ወንድሞች ህይወት ያላቸውን ወደ ህክምና የሞቱተትን አስከሬን ወደ ቤት ለመውሰድ የመጡትም የወያኔ ቅልብ ቅጥር ነፍሰ ገዳይ ጥይት ሲሳይ ሆነው ቀሩ::ከአንድ ቤት ሁለት እና ከዚያም በላይ ተገደሉ::

ዳግማዊ ደርግ የሆነው የወያኔ አረመኔ ቡድን የገደላቸውን ሰዎች አስከሬን እየለቀመ ወደ ምኒልክ ሆስፒታል እየወሰደ በአንድ ሰው አስከሬን ከ1 ሺህ ብር በላይ እንዲከፍሉ አድርጎዋል፡፡

ድምጻችን ይከበር ብለው ባዶ እጃቸውን ለሰላማዊ ሰልፍ የወጡ ወጣቶችን እያሳደዱ በጥይት ከመደብደባቸውም በላይ ባንክ ሊዘርፉ ሲሉ ተገደሉ እያለ የወያኔው ቡድን ሲገልፅ ነበር የዋለው፡፡አዎ ያቺ የተረገመች ሰኔ 1ቀን ዕለተ ሐሙስ ስንቱን ንጹህን ዜጎቻችንን ቀረጠፈች?

ይህን የመሰለ ግፍ የተፈጸመባቸውን ዜጎች ለማስታወስ እና ለመዘከር ነበር መኢአድ ቢሮ የሙዋች ቤተሰቦች የታደሙት፡፡ዕለተ ማክሰኞ ሰኔ 1 ቀን 2002 ዓ.ም 5ኛ ዓመት የሰማዕታት ቀንን ለማክበር በመኢአድ መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ የተገኙ የሙዋች ቤተሰቦች የሻማ ማብራት ስነስርዓት እንዲያደርጉ አንዲት የሙዋች እናት ተጋበዙ .......ግና አላስቻላቸውም ......ያችን ዕለት አስታውሰው እንባቸውን መቆጣጠር አቃታቸው እናም ምናለበት ምንም ያልያዙ ህጻትን በአርጩሜ ወይም በዱላ ቢመቱዋቸው ?እያሉ በቁጭት አለቀሱ...... ከዛማ አዳራሹ ሁሉ በለቅሶ በሀዘን ተዋጠ፡፡

አንዱ የአንዱን አንገት እያቀፈ መላቀሱ ቀጠለ...... በሁዋላ ሁሉም የመጡት ለማልቀስ ሳይሆን ለማስታወስ መሆኑ ተነግሮዋቸው ስነ ስርዓቱ ተጀመረ፡፡በዘንድሮው በዓል ላይ አንድ ትልቅ መልዕክት ተላልፎዋል፡፡ይሄውም «የቀይ ሽብር ሰማዕታት ሀውልት ተሰርቶ ተመርቆዋል፡፡የእኛም ልጆች እና ወንድሞች የሞቱበትን ሰኔ 1ቀን 1997 ዓ.ም ለማስታወስ የሰማዕታት ሐውልት እንዲሰራላቸው» ሲሉ ጥሪ አቀረቡ፡፡

አዎ በግፍ የተገደሉት ሰማዕታቶች ሐውልቱ ሊቆምላቸው ግድ ይላል ......ግን ይሄ ታዲያ ወያኔ ሲወገድ የሚሆን እንጂ አሁን የሚታሰብ አይደለም ሲሉም አንድ የመኢአድ ከፍተኛ ባለስልጣን ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

አንዲት የሙዋች እናት ደግሞ እንዲህ አሉ «እኔ በጣም የሚቆጨኝ ልጅሽ የተገደለው ባንክ ሊዘርፍ ሲል ነው ብለው የሰጡኝ ምክያት ነው፡፡እስቲ ይታያችሁ የ12 ዓመት ህጻን ባዶ እጁን ባንክ ሊዘርፍ ሲል ተገደለ ተብሎ መግለፅ የሰው ልጅ እንደ ጉዋሮ አትክልት ቆርጦ መጣል ለወያኔ ምን ያህል ቀላል እንደሆነ ወገኖቼ ተረዱኝ »በማለት ነበር በእንባ ፊታቸውን እያጠቡ የገለፁት፡፡

ቀጠለና ደግሞ አንድ ስሙ እንዲገለጽ ያልፈለገ የሙዋች ወንድም እንዲህ አለ «የእኛ ወንድሞች አልሞቱም ምንግዜም ህያው ሆነው ሲታወሱ ይኖራሉ የሞቱት ግን የወያኔ ባለስልጣናት እና ቅጥር ነፍሰ ገዳዮቹ ናቸው፡፡ዛሬ እዚህ የተገኘነው ልናስታውሳቸው በመሆኑ ማልቀስ አይገባንም...... በቅርቡ ከህዝቡ ጋር ሆነን እንባችንን እምናብስበት ታሪክ እንሰራለን...... አይዞችሁ!...... አይዞችሁ!....» እያለ ነበር በእልህና በወኔ ሲናገር የነበረው፡፡

ዛሬ ወያኔ ዙሪያው ገደል በሆነበት በአሁኑ ወቅት ያለፈውን ስህተት ከመድገም ወደ ሁዋላ የማይል ቡድን መሆኑንም በዘንድሮው ምርጫም አሳይቶዋል፡፡በመሆኑም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች

ውስጥ ሰዎችን እየገደለ እንደ አልባሌ በየጉድጉዋድ ውስጥ እየጣለ መሆኑንም ከተለያዩ ቦታዎች የሚደርሱን ጥቆማዎች ያስረዳሉ፡፡

ዛሬም ከበረሀ ታጋይነት ስሜት ያልተላቀቁት የወያኔ ነባር እና ከፍተኛ ባለስልጣናት በተለይ የህወሀት ባለስልጣናት ደማችን አፍስሰን...... አጥንታችንን ከስክሰን....... ያመጣነው ውጤት በመሆኑ ውስኪ እንጠጣለን ስንፈልግ እንደፋዋለን እያሉ ሲደነፉ እየተደመጡ ነው፡፡

በውሸት እና በማጭበርበር የህዝብ ድምጽ ሰርቀው አሸነፍን ያሉት የወያኔ ባለስልጣናት የደስ ደስ በሚል በተለያዩ አዳራሾች ድል ያለ ድግስ እያዘጋጁ በጮማና በውስኪ እየተራጩ ከመሆኑም በላይ ዛሬም ከ19 ዓመት በፊት የነበራቸውን ስሜት በህዝቡ ላይ እያንጸባረቁ መሆኑንም ከውስጥ አዋቂ ምንጮች ያገኘነው ጥቆማ ያስረዳል፡፡

በመንገድ ትራንስፖርት አዳራሽ ውስጥ ባለፈው ሳምንት የምርጫውን ማሸነፍ ምክንያት በማድረግ በሚል የሚኒስቲር መስሪያ ቤቱን አባል ሰራተኞች እና ቤተሰቦቻቸውን ሰብስበው ውስኪ እንደ ውሀ እየተደፋ......ጮማ እንደ ቅጠል እየተጣለ..... ድል ያለ ድግስ ከማዘጋጀታቸውም በላይ ባለስልጣናቱ በስካር መንፈስ «ከበረሀ ደምተን የመጣነው ለዚህ በመሆኑ አይዞን ጠጡ ብሉ» እያሉ ሲለፋደዱ መደመጣቸውን ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

ህዝቡ ወያኔ በፈጠረው ችግር ምክንያት ኑሮው ህልውናውን እየተፈታተነ ባለበት በዚህ ወቅት የወያኔ ባለስልጣናት ግን በሰበብ አስባቡ ግብዣ እያዘጋጁ በህዝብ ሀብት እየቀለዱ ከመሆናቸውም በላይ ዛሬም በበረሀ ስሜት ህዝቡን ማስፈራራታቸው የሚያሳዝን ከመሆኑም በላይ የሚያሳፍር ነው ሲሉ ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል፡፡

ረሀብተኛው ቁጥር በየቀኑ እያሻቀበ ነው እየተባለ በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ሳይቀር እየተገለፀ ባለበት በዚህ ቀውጢ ወቅት ነባር እና ከፍተኛ ባለስልጣናቱ ተስፋ ከመቁረጥ የመነጨ ስሜት ህዝቡን እያስፈራሩ በጥፋት ላይ ጥፋት እየፈጸሙ መገኘታቸው ሀገሪቱን እና ህዝቡን አውላላ ሜዳ ላይ ጥለው ሊጠፉ የተዘጋጁ ይመስላል ሲሉም ምሁራኖች ሲተቹ ተደምጠዋል፡፡

ለ2003 ዓ.ም ወያኔ ያፀደቀው ባጀት 77 ቢሊዮን ብር ነው ያሉት ምሁራኖቹ ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ግማሽ ያህሉ ለወያኔ የስልጣን ማራዘሚያ የሚጠቀምባቸው መሆኑን ጨምረው ገልፀዋል፡፡በብድር እና በእርዳታ የሚመጣውን ገንዘብ ለዓመታዊ በጀት መድቦ የሚንቀሳቀሰው ወያኔ ከባጀቱ ግማሽ ያህሉ ለመከላከያ፤የፌዴራል ፖሊስ እና የደህንነት ተቋዋም ማጠናከሪያ የሚውል ነው ሲሉም አክለው ገልፀዋል፡፡

በመጨረሻም በቅርቡ የተደረገውን ምርጫ አስመልክቶ ወያኔ ሙሉ ለሙሉ ያሸነፈ በመሆኑ አምናችሁ ያለ አንዳች ክርክር እና ውዝግብ መቀበል አለባችሁ እያሉ ከዚህ በፊት ለወያኔ ቀኝ እጅ ሆነው ሲሰሩ የነበሩት ሽማግሌ የተባሉት ግለሰቦች ማስፈራራት መጀመራቸውን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አስታወቀ፡፡

እንደ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ ከሆነ በቅርቡ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የምርጫ ውጤቱን በግዴታ እንዲቀበሉ የሀገር ሽማግሌዎች ናቸው የተባሉት እነ ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሀቅ እና ፓስተር ዳንኤል የተባሉት እያስገደዱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ለወያኔ ጭንቅ ግዜ ደራሽ የሆኑት እነዚህ የሀገር ሽማግሌ ናቸው የተባሉት ግለሰቦች ለወያኔ በሚመች ሁኔታ  እራሳቸው ፅፈው ያዘጋጁት ህግ ላይ የፓርቲ መሪዎች ፊርማና ማህተም እንዲያደርጉበት ጫና ከማሳረፋቸውም በተጨማሪ ይህንን ያላደረገ እንደ 1997 ዓ.ም ጊዜው ወደ እስር ቤት ሊገባ ይችላል እያሉ እንደሆነም ምንጮቹ ጠቁመዋል፡፡

ምንም እንኩዋን እነ ኤፍሬም ይስሀቅ 14 ብጥስጣሽ ፓርቲ መሪ ናቸው የተባሉትን በግዴታ አስፈርመውና ማህተም ያስደረጉ ቢሆንም መድረክ እና መኢአድ ምርጫው ተጭበርብሮዋል ይደገም የሚል ጥያቄ በማቅረባቸው ጭምር የሽማግሌዎቹን ሀሳብ አንቀበልም በማለት አሳፍረው መመለሳቸውን ጨምሮ የደረሰን ጥቆማ አብራርተዋል፡፡